የሰ/መ/ቁ 48967

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሳዲቅ ሐሰን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ

አቶ ጌታነህ ቸሬ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ለውጭ አገር የተደወለ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር መስከረም 2004 ዓ.ም ድረስ የተጠቀመበትን ብር 19,793.52(አስራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሃምሳ ሁለት ሣንቲም) እና የስልክ ቀፎ ዋጋ ብር 249.55(ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ አምስት ሣንቲም) በድምሩ ብር 20,043.07 (ሀያ ሺ አርባ ሶስት ብር ከሰባት ሣንቲም) የስልክ አገልግሎት ክፍያና የቀፎ ዋጋ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የተጋነነ ሒሳብና ያልደወሉበት የውጭ አገር የስልክ ሒሳብ የተጠየቁና ይኸም በኮንፒዩተር ስህተት የመጣ መሆኑን በመግለፅ ጉዳዩ እንዲመረመር ለአመልካች መሥሪያ ቤት ያመለከቱ መሆኑንና በዚህ መሠረት የታህሣሥ ወር ክፍያ ተመርምሮ ከብር 891.25(ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ወደ ብር 92.26 (ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም) ዝቅ ያለ መሆኑን ገልፀው ሒሳቡ ሣይመረመር በዓለም ላይ ወደ ሌላ አገር USSR ደውለሀል ተብዬ መከሰሴ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የታህሣሥ ወር በአማካኝ ክፍያ እንዲፈፅሙ ስለተደረገ እንጅ ተመርምሮ ስህተት በመሆኑ ሒሳቡ አልተቀነሰም የተገለገሉበትን ስልክ ዋጋ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የጠየቅሁት የስልክ ግልጋሎት ክፍያ በኮንፒዩተር ስህተት ምክንያት ተጋንኖ የተጠየቀ ነው፡፡ ይኸ እንዲመረመርልኝ ያቀረብኩት አቤቱታ በመቀበል እንዲመረመር ሣይደረግ ተጠሪ የጠየቀውን ሂሳብ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ያቀረብነው ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የጠየቀው የስልክ ግልጋሎት ዋጋ የተጋነነ በኮምፒዩተር ስህተት የመጣ ነው የሚለውን የአመልካች አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ በባለሙያ ሣይመረመር ተጠሪ የጠየቀውን ሂሳብ በሙሉ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የስልክ መስመሩ ተገልጋይና የስልክ ቀፎው ባለይዞታ መሆኑ በእሱ ስልክ ቁጥር ወደ ውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ የተደረገው የስልክ ግንኙነት በእሱ የተፈፀመ ነው የሚል ግምት የሚያሣድር ነው፡፡ ሆኖም አመልካች የተጠየቀው የስልክ ግልጋሎት ዋጋ ከወትሮው የተለየና የተጋነነ መሆኑን አመልካች እስከ አዲስ አበባ ዋናው መሥሪያ ቤት ድረስ ያመለከተ መሆኑንና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የታህሳስ ወር 2003 ብር 891.25(ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ተጠይቀው የነበረውን 92.26 /ዘጠና ሁለት ብር ከሀያ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፍል መደረጉን አመልካችና ተጠሪ አልተካካዱም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የተለያዩበት ዋናው ነጥብ አመልካች ኮንፒዩተሩ ተመርምሮ ስህተት ሆኖ በመገኘቱ በፊት የተጠየቅሁት ገንዘብ ተቀንሶ ከፍያለሁ ሲል ተጠሪ በበኩሉ በአቨሬጅ ወጥቶና በዚያ መሠረት ተሰልቶ ነው እንዲከፍል የተደረገው በማለት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሚካካዱበት ምክንያት ቢሆንም እንደ አውሮፓሮውያን አቆጣጠር ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቀው የስልክ ግልጋሎት ክፍያ አመልካች በደንበኝነት በቆዩበት ጊዜ ይከፍሉት ከነበረው አቬሬጅ ክፍያ በየወሩ ስምንት እጥፍ ብልጫ ያለውና የተጋነነ በመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸንንም ሁኔታ በመቃወም አመልካች እንዲመረምርላቸው ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች የተገለገለበትን የስልክ ግልጋሎት ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን በተነፃፃሪው ተጠሪ የአመልካች የስልክ መስመር ከአመልካች ውጭ ሌላ ሰው እንዳይገለገልበት ተገቢውን ጥበቃና ጥንቃቄ የማድረግና አመልካች ላገኘው ግልጋሎት የአገልግሎት ዋጋ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ተጠሪ ደንበኞቹ የተጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ ትክክለኛነት በሚጠይቁበት ወቅት የማስመርመሪያ ገንዘብ ከፍለው እንዲመረመር የሚያደርግ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ያላቸው የውል ግኑኝነትና በውል አፈፃፀም የሚነሡ ችግሮች በመጀመሪያ ተጠሪ በልምድ ባዳበረው አሠራር መሠረት መታየትና መጣራት ያለበት ነው፡፡ ይኸም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሊኖር የሚገባው ግኑኝነት ቅንነትንና መተማመንና በጉዳዩ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል ሊፈታ የሚገባው በመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1732 ድንጋጌ ለመገንዘብ ስለሚቻልና ተጠሪ ደንበኞቹ የተጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ የተጋነነ ነው ወይም ጥሪ ያላደረግሁበትን የውጭ አገር ስልክ አገልግሎት ዋጋ እንድከፍል ተጠይቄአለሁ በሚሉበት ወቅት ደንበኞቹ የተወሰኑ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመረመርበት በልምድ የዳበረ አሠራር ያለው በመሆኑ ተጠሪ ኢ.ኤ.አ በታህሳስ ወር 2003 የተጠየቀው ሂሳብ የተጋነነ መሆኑን አቤቱታ ሲያቀርብ ተገቢው ምርመራ ማድረግ ሲገባው ምርመራ አለማድረጉና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከጥር ወር 2003 እስከ መስከረም 2004 ድረስ ያለው ሒሳብም ሣይመረመር አመልካች እንዲከፍሉ መጠየቁና የበታች ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ዕውነታው ሣይረጋገጥ ተጠሪ የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች ሙሉ በሙሉ እንድከፍል መወሰናቸው አመልካችን ግዴታና ኃላፊነትና በልምድ የዳበረውን የተጠሪን አሠራር ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለማስመርመር የሚገባውን ግዴታና ኃላፊነት እንዲወጣ በማድረግና የአመልካች መስመር እንዲመረመር በማድረግ በሚቀርብለት ውጤት መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ